# የቁሮ ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አህመድ ተጠያቂ ነው

ዘውዲቱ የማነ
2019-10-05

የቁሮ ጠቅላይ ሚንስትር ኮሎኔል አብይ የአንድነትና የዲሞክራሲ ጠላት መሆኑን በተለያየ መንገድ እያሳየ፣ አብይ አይደለም የተሳሳተው የመከላከያው ብርሀኑ ጁላ ነው፣ አብይ አይደለም የተሳሳተው የኦዴፓ ምክትል ሊቀመንበር ሽመልስ አብዲሳ ነው፣ እያላችሁ አብይን ንፁህ ለማድረግ የምትጥሩ ተደማሪዎች በዚህ አስተዛዛቢ ቀን ታዘብናችሁ። አስመሳዩ አብይ አህመድ አማራን በገጀራ ሲጨፈጭፉ፣ ነፍሰጡር፣ ህፃንና መለኩሴ ሳይመርጡ ሲያርዱ የኖሩትን አነጋውያን በመደመር ስም አቅፎ ድገፎ መያዙ ሳያንስ ቡራዩ ላይ ያን ሁሉ ንፁህ ህዝብ ሲደፍሩ፣ ሲያርዱ ቤት ሲያቃጥሉ ዝም አለ። አሁን እሱ ስልጣን ከያዘ ወዲህ ከ 15 በላይ ቤተክርስቲያን ሲጋዩ፣ መነኮሳትን፣ ምእመናንን በአሰቃቂ ሁኔታ አረዱ ። ሌላው ቢቀር የእሱ የራሱ ባለጊዜ ባለስልጣናትም ኦሮሞ ያልሆነ ህዝብን ተወልዶ ካደገበት፣ በሰላም ከሚኖርበት ቤትና አካባቢ ሲያፈናቅሉ የእሱ እጅ የለበትም እንዴት ይባላል?

በጥጋብ ልባቸው የተደፈነውን የኮሎኔል አብይ ባለስልጣናት ለሚቀባጥሩት ሁሉ ሀላፊነት ሳይወስድ ተጠያቂ ሳያደርግና ከስልጣን ሳያወርድ፣ ዝም ማለቱ ኢትዮጵያዊያንን መናቁን ማሳያ ነው። ይባስ ብሎ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በተረኛና ነውረኛ ታጣቂዎች ሲዋረድ ዝም ብሎ ሳምንት ሳይሞላው የአነግን ጨርቅ መፍቀዱ መሰሪነቱን ማሳያ ነው። ቀን የሰጠው አብይ አህመድ አሸባሪው ጁሀር ጋር እየተሞዳሞደ ሰላማዊው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ላይ ጦር እንማዘዛለን ብሎ ያስፈራራውንስ ከግንዛቤ ውስጥ አለማካተትና ምንም እንዳልሆነ ንቆ መተው እንዴት ይቻላል።

ፕሮፌሰር አስራትን አብሮ አጨብጭቦ ያስገደለው፣ ባለስልጣኖቹ አይኑ እያየ ሲጠፉ አብሮ ተባብሮ አስመትቶ አ ተከላካይ አለኝታችንን ጀኔራል አሳምነው ፅጌን መፈንቅለ መንግስት ሙከራ አደረገ ብሎ የከሰሰውና የገደለው/ያስገደለው ወያኔ የተከለው፣ ኦዴፓ የሚባል አስጠቂ ድርጅት መቸም ቢሆን የአማራ ስነልቦና ተላብሶ አያውቅም። ሽቁጥቁጥ አሽከር ስለሆነ በየሄደበት ይመዋረዱን እንደልብሱ ቆጥሮታል። አማራን የመወከል አቅም መቸም አያገኝም። ኢትዮጵያንም ከተጋረጠባት መከራ የሚታደጋት መከራ ያንገፈገፈው ህዝብ እንደህዝብ በፅናትና በህብረት በጋራ ሲቆም ብቻ ነው።

ኢትዮጵያን ሊያጠፉ ደከሙ በከንቱ

ተለማምጠው ገብተው ፎከሩና ዛቱ

አከርካሪ መትተን ጣልን ማለታቸው

ያዳቆነው ሰይጣን እያቀሰሳቸው

በጥጋብ መደንፋት ማቅራራት አበዙ

በጋራ ለመኖር ልቦና ያልገዙ

ገዝቶ አያውቅ አይግዛ ሆነና ነገሩ

ጠዋት ማታ ተነስተው ህዝብ ያሸብራሉ።

ማስተዋል መታገስ መች ሆነና ፍራት

በኢትዮጵያ ከመጣ ገፍቶ ይሞከራት።